# የተላከብን ጦስ

ሃይማኖት ሊያጠፋ ፣ ሊነዳ ፣ እንጦሮንጦስ
ባገር የዘመተ ፣ የተላከብን ጦስ
ተመስሎ መጥቶ ፣ ዛሬ ፣ በአባ ጳውሎስ
ቤተ መቅደስ ገብቶ ፣ ቁጭ ብሏል ፣ ዲያቢሎስ ።

በሳጥናኤል ልዑክ ፣ በዲያቢሎስ አባ
ገዳም ይቃጠላል ፣ ይፈርሳል ዋልድባ
እንደ ጎርፍ ፣ ይፈሳል ፣ የምዕመን እንባ
ነፍሱ ሳትለየው ፣ በምድር ፣ ሲያል ገባ ።

በግ መሃል ፣ የገባ ፣ ተናካሽ ቀበሮ
መስቀሉን ደብቆ ፣ ሽጉጡን ቀርቅሮ
በቢዮንሴ ዘፈን ፣ ዳንኪራ ጨፍሮ
ቤተ መቅደስ ፣ ገብቶ ፣ ያቀረሻል ሰክሮ
ህገ ክርስትና ፣ ዛሬ መች ፣ ተከብሮ
ሰው መስሎ ፣ መጣብን ፣ ሳጥናዔል ዘንድሮ ።

በናባ ዲያቢሎስ ፣ አቲዮ ፣ ባቲዮ ፣ እየተቀደሰ
በአጋንንት ሹሞች ፣ በናቶ መለሰ
አገርና ድንበር ፣ ሄደ ተቆረሰ
መኩሪያ ታሪካችን ፣ ሁሉም ፈራረሰ
አሰቦት ዝቋላ ፣ ተቃጠለ ጨሰ
ህዝበ ክርስቲያኑ ፣ ደም ዕንባ ፣ አለቀሰ
ትንቢት ተፈፀመ ፣ ሰዓቱም ደረሰ
ባገር ፣ በመቅደሱም ፣ ዲያቢሎስ ነገሰ ።

ቀንዱን መሸፈኛ ፣ ቁልል ቆብ ፣ አጥልቆ
በቀሚሱ ጋርዶ ፣ ጭራውን ደብቆ
መቀነት ይመስል ፣ ዙሪያ ፣ ዝናር ታጥቆ
በክርስትና እምነት ፣ መጣ ፣ ጦሩን ሰብቆ
ፈጀው አቃጠለው ፣ በዕቶን አጥምቆ ።

እሾህ አሜኬላ ፣ ታሪክ አደፍራሹ
የተናቀን ወዳጅ ፣ የተተፋ ላሹ
በቢዮንሴ ዜማ ፣ ዘማሪ ቀዳሹ
ማሽብሸቡን ትቶ ፣ ማርንጌ ደናሹ
ዲያቢሎስ ታላቁ ፣ ጳውሎስ ነው ፣ ታናሹ ።

ከጨለማው ንጉስ ፣ የምድሩ ተጠሪ
አባ ተልኮልን ፣ ለኛ ፊታውራሪ
የቤተ ክህነቷ ፣ አዛዥ ፣ ሿሚ ፣ ሻሪ
በየገዳማቱ ፣ ሆኗል ፣ እሳት ጫሪ
ህዝበ ክርስቲያኑን ፣ ያሳኘዋል እሪ ።

ታዛቢው ... April, 02, 2012

EthioLion.Com